**ጌታ ኢየሱስን ለማየት ወደ ከፍታ መውጣት** (ሉቃ 19፡1-10፣)

ከክፍሉ መረዳት እንደሚቻለው ዘኬዎስ የተባለ በኢያሪኮ አካባቢ ቀረጥ ሰብሳቢዎች ኃላፊ የነበረ ሰው ስለ ጌታ ኢየሱስ ማንነትና ዝናው ሰምቶ በሰማው ነገር ምክንያት በጌታ ኢየሱስ ተግባራት የተደነቀ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ከተቻለ እርሱን ማየትና በቅርበት/በአካል ለማወቅ በጣም ፈለገ፡፡ እንዲህ ዓይነት የምህረት ጌታ ባገኘሁት፣ ፊት ለፊት ባየሁትና ባወቅሁት ወዳጄ በሆነ ብሎ የተመኘ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በቤቱ አቅራቢያ ሊያልፍ ቢመጣም ብዙ ሰዎች ዙሪያውን ከበውት ስለበሩና ዘኬዎስም ቁመቱ አጭር ስለነበረ ጌታን ማየት የማይችልበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስን ለማየት የሚያስችለው መንገድ ፈልጎ በሚያልፍበት መንገድ ላይ ወዳለ ሾላ ዛፍ/ከፍታ ላይ ሂዶ ወጣና ኢየሱስ እስኪቀርብ ተጠባብቆ ፊት ለፊት ማየት ቻለ፡፡

ጌታ ኢየሱስም እርሱን ማወቅ የሚፈልገውን ይፈልግ ስለነበር ሾላው ጋ እንደ ደረሰ ቀና ብሎ አይቶት ጠራውና ወደ ቤቱ ሊገባ ፈቃደኛነቱን ገለጠለት፡፡ (ሆሴ 6፡6 ከመስዋዕት ይልቅ ምህረትን፣ ከሚቃጠል መስዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅን እሻለሁና) እግዚአብሔር ሊያውቁት የሚፈልጉትን ይፈልጋል፡፡ ዘኬዎስ ኢየሱስን የፈለገው ለሆነ ጉዳይ ሳይሆን ራሱ ኢየሱስን ለማወቅና ቢቻል ከእርሱ ጋር ቀረቤታ እንዲኖረው እንደተመኘው ሆነለት፡፡

ዘኬዎስ ፈጥኖ ከሾላው ወረደና ቤቱንና ልቡን ለኢየሱስ ከፍቶ፣ በደስታም ተቀብሎ አስተናገደው፣

ዘኬዎስ በሰዎች እይታ፡ - በዚያን ጊዜ እንደ ዘኬዎስ ቀራጭ የሆኑ ሰዎች አንድ የተወሰነ አካባቢ ከሮማውያን ቅኝ ገዢዎች ግብር የመሰብሰብ ኃላፊነት ይቀበሉና ለሮማዊያኑ ሊያስረክቡ ከተዋዋሉት ግብር በላይ ከህዝቡ በመሰብሰብ ትርፉን ለራሳቸው በማስቀረት ጠቀም ያለ ገቢ ያገኙ ስለነበር ሰዎች ህዝቡን ይበዘብዛሉ በሚል እንደ ኃጢአተኛ ይቆጥሯቸው ነበር፡፡

ዘኬዎስ እዚያ በነበሩ ሰዎች እይታ ኃጢአተኛና እንደ ለምጻም የሚቆጠር ስለ ነበር፣ ኢየሱስ እንዴት ኃጢአተኛ ቤት ገብቶ ይስተናገዳል በማለት አጉረመረሙ፡፡

ዘኬዎስ በኢየሱስ እይታ/የኢየሱስ ምላሽ …. ዘኬዎስ እርሱን ለማወቅ ያለው ጥማት አይቶና ስራው ቀረጥ መሰብሰብ ቢሆንም ያለብዝበዛ በአግባቡ የሚሰራ ብቻ ሳይሆን ለድሆች ብዙ ቸርነት ያደርግ የነበረ መሆኑን በተናገረ ጊዜ፣ መዳን ለዚህ ቤት ሆኗል አለው፤ ታላቅ መዳን ለራሱና ለቤተሰቡ ሁሉ ሰጠው፣ ፊቱን እንዲያይ፣ ድምጹን እንዲሰማ፣ ቤቱ ገብቶ እንዲስተናገድና በቅርበት እንዲያውቀው አስቻለው፡፡ ጌታ ኢየሱስ ወዳጅ ሆነው፡፡

<u>ጌታን በሌሎች ሰዎችም ሆነ በራሳችሁ ሕይወት ባደረገው የማዳን የመባረክና ከክፉ የመጠበቅ ስራ የተደሰታችሁ፣ የተደነቃችሁ፣ የወደዳችሁት፣ ይበልጥ ልታውቁት የምትፈልጉ እሱም ስለሚፈልጋችሁ ጌታን ታዩታላችሁ፡፡</u>

በአዲስ ኪዳን ሌሎች ኢየሱስን ማየት የፈለጉ ሰዎችና ምክንያታቸው እንመልከት፡-

ሉቃ 9፡8-9፣ 23፡6-11፣ ሄሮድስ ጌታ ኢሱስ ተአምራት ሲያደርግ ማየት ይፈልግ ነበር (ቲያትር በማየት እንደመዝናናት…. ኢየሱስም ታምራት ማድረግ ስላልፈለገና ስላላደረገ ናቀው

ዮሐ 6፡14-25-27፣ ከባህሩ ማዶ ባገኙት ጊዜ፣ ረቢ መች ወደዚህ መጣህ አሉት፡፡ ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡፡ እውነት እላችኋለሁ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለበላችሁና ስለጠገባችሁ እንጂ ታምራዊ ምልክቶችን ስላያችሁ አይደለም አላቸው፡፡ ነገር ግን ትኩረታችሁ የሰው ልጅ በሚሰጣችሁ የዘላለም ሕይወት ላይ እንጂ በሚጠፋ እንጀራ ላይ አይሁን አላቸው፡፡ ቀድሞ በነበሩበት ሁኔታ እየተመላለሱ እርሱም ማን እንደሆነ ሳያውቁት ታምራት እየሰራ እንጀራ እያበላቸው ስራ ፈት ሊያደርጋቸው አልነበረም፡፡ ጌታ ማንም ያላደረጋቸው ታምራትን ያደርግ የነበረው እግዚአብሔር ይመጣል ብሎ የተስፋ ቃል የሰጠው መሲህ መሆኑን እንዲታወቅና ሁሉም በእርሱ በማመን እንዲድኑ ነበር፡፡

- ዘኬዎስ ጌታ አጠገቡ እያለ ሊያየው የከለከለ ነገር እንደነበር ዛሬም እኛ አጠገባችን እያለ እንዳናየው የሚከለክሉ ነገሮች አሉ፡፡ (የሰዎች ሁኔታ ማየት፣ አግዝፈን የምናያቸው ልዩ ልዩ ችግሮቻችን …)፡፡
- ጌታን በሚያስፈልገን ጊዜና ጉዳይ ሁሉ (በአገልግሎታችን፣ በግል ጉዳዮቻችን) ማየት ይቻላል ወይ፡፡ አዎን ይቻላል፡፡ ግን ከፍታ ላይ መውጣት ይጠይቃል፡፡ ከፍታ ላይ መውጣት ያደክማል/ቀላል አይደለም፡፡ ቀላል ቢሆንማ ኖሮ ሁሉም ሰው ያደርገው ነበር፡፡ ቀላል ባይሆንም ሁሌ አሁን ካለንበት ሁኔታ እልፍ ሳንል ከምንቀር ከዚያም አልፎ የኋልዮሽ እንዳንሄድ ጌታ ክብሩን በህይወታችን እንዲገልጥ ከፍታ ላይ መውጣት ይሻለናል፡፡

ዘኬዎስ ጌታን በአካል/ፊዚካል ቦዲ ለማየት ፊዚካል ከፍታ/ሾላ ላይ ወጣ፡፡ ሙሴም እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ተገልጦለት ያየው በኋላም 40 ቀንና ሌሊት የእስራኤል ህዝብ ሊከተለው የተገባውን ስርዓት ያስተማረው/ ያሳየው ተራራ ከፍታ ላይ ነው፡፡

እኛ አሁን መንፈስ የሆነውን ጌታ ለማየት ቁሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ከፍታዎች ላይ መውጣት ያሻናል፡፡

አሁን በኛ ዘመን ዘኬዎስ ጌታን በአካል ስጋ ለብሶ ፊት ለፊት እንዳየው ማየት አንችልም፡ ፡ ግን ጌታን አየሁ የሚባለው በአካል ስላዩ ብቻ አይደለም፡፡ ኢዮብ እግዚአብሔርን በአይኔ አየሁ ያለው ድምጹን ስለሰማና እግዚአብሔር ብቻ ሊሰራቸው የሚችሉ ድንቅ ስራዎች በራሱ ሕይወት/ኑሮ ሰርቶለት ስላየ ነው፡፡ ዛሬም ጌታ ለኛ በድምጹ ሊናገረን፣ በራዕይ/በህልም ሊታየን በከበዱን የጠላት ውጊያዎች ላይ በድንቅ ታምራዊ ስራው ሊገለጥልን…ወዘተ ይችላል፡፡

እግዚአብሔር በመልካምነቱ ባለጠጋ ስለሆነ ጌታን በማያምኑ ሰዎች ሕይወት ሳይቀር ለብዙዎች ብዙ መልካም ነገር ሊያድርግ ይችላል፡፡ ዛሬ ብዙዎች በዓለም ሁሉ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚሉ ከዓለማውያን ተለየ የሚባል ባህርይ የሌላቸው ሞልተዋል፡፡ ነገር ግን እርሱን ለማየት ከፍታ ላይ ለሚወጡ ሁሉ በእርግጠኝነት መልካም ነገር እንደሚያደርግላቸው የተስፋ ቃሉን ሰጥቷል፡፡

እነዚህ መንፈሳዊ ከፍታዎች ምንድናቸው፡-

1. ናሆ 1፡15፣ እነሆ ሰላምን የሚያመጣው፣ ሰላምን የሚያውጀው ሰው እግር በተራሮች ላይ ነው፡፡
   ኢሳ 52፡7፣ በተራሮች ላይ የቆሙ የምስራች ይዘው የሚመጡ እግሮች፣ ሰላምን የሚናገሩ መልካም ዜናን የሚያበስሩ፣ ድነትን የሚያወጁ፤ ጽዮንንም አምላክሽ ነግሷል የሚሉ እንዴት ያማሩ ናቸው፡፡
   ሮሜ 10፡14-15፣ ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው ይጠሩታል? ስለ እርሱ ሳይሰሙ እንዴት ያምናሉ? ያለ ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ? ካልተላኩስ እንዴት መስበክ ይችላሉ፡፡ መልካሙን የምሥራች የሚያመጡ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡

   አገልጋዮች የሆናችሁና የሙሉ/የከፊል ጊዜ የወንጌል አገልጋዮች ባትሆኑም በክርስቶስ ኢየሱስ አዳኝነት አምናችሁ የዳናችሁ ሁሉ የእግዚአብሔርን ታላቅ ስራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉስ ካህናት ስለሆናችሁ በተገኙ አጋጣሚዎች ሁሉ ወንጌልን ላልሰሙት በማሰማት የእግዚአብሔርን በጎነት ለመናገር የምትለማመዱ ቀኖሉበት እግዚአብሔርን ታዩታላችሁ ፡፡
2. የእግዚአብሔርን ቃል (ፈቃድ) በመተግበር/በመታዘዝ፡-
   መዝ 24፡3-4-6፣ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ሊወጣ ይችላል፡፡ በተቀደሰው ስፍራስ ማን ይቆማል፡፡ ንጹህ እጅና ቅን ልብ ያለው፣ ነፍሱን ለሀሰት ነገር የማያስገዛ፣ በውሸት የማይምል፤ እርሱ በረከትን ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትንም ከአዳኙ አምላክ ይቀበላል፡፡

   ኢሳ 33፡15-16፣ በጽድቅ የሚራመድ ቅን ነገር የሚናገር፤ በሽንገላ የሚገኝ ትርፍ የሚንቅ፣ መማለጃን ላለመቀበል እጁን የሚሰበስብ፣ የግድያ ሴራ ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፣ ክፋትን ላለማየት አይኑን የሚጨፍን፡፡ ይህ ሰው በከፍታ ላይ ይኖራል፡፡ የተራራም ምሽግ መጠጊያው ይሆናል፡፡ እንጀራ ይሰጠዋል ውሃውም አይቋረጥበትም…፡፡ ማቴ 5:6-8፣ ዕብ 12፡14;

   Jn 14፡15-17፣ ብትወዱኝ ትዕዛዜን ትጠብቃላችሁ፡፡ እኔ አብን እለምናለሁ እርሱ ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፡፡ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው …፡፡
   21፣ የሚወደኝ ትዕዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ፡፡
   23፣ የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፣ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እንኖራለን፡፡

   1ኛ ሳሙ 15፡22-23፣ ሳሙኤልም እንዲህ አለ፤ “ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃጠል ቍርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ! መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል።
   23 ዐመፅ እንደ ጥንቈላ ያለ ኀጢአት፣ እልኸኝነትም እንደ ጣዖት አምልኮ ያለ ክፉ ነገር ነው።…”

እግዚአብሔር ከሰው ከሚፈልጋቸው ነገሮች ዋነኛው፣ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ተግባራዊ በማድረግ፣ ከኃጢአት በመራቅ፣ በቅድስና በመመላለስ ጸንቶ እንዲኖር ስለሆነ፤

በእንዲህ ዓይነቱ ሰው ደስ ስለ ሚሰኝበት በበረከት ላይ በረከት በመጨመር እንዲባረክ በማድረግ ጠላቶቹ እያዩ ከፍ ከፍ እንዲል ያደርገዋል፡፡ ከእምነት በመነጨ ፍቅር ኢየሱስን ከመውደድ የተነሳ ፈቃዱን ለማድረግ የምትጠሙና የምታደርጉ ይህን መልካም ጅምራችሁን አሳድጉ፡ ፡ ጌታም በጉዳያችሁ ላይ ራሱን መግለጥ ይጀምራል፡፡

እነ መግዳላዊት ማርያም ኢየሱስን አካል ሽቶ ለመቀባት ጉዞ ሲጀምሩ መሰናክል የሆነ መቃብሩ የተዘጋበት ድንጋይ መኖሩን ቢያውቁም ጉዞዋቸውን አላቋረጡም፣ ሽቶውንም አልተውም፣ የኢየሱስና የተከታዮቹ ተቃዋሚ ፈሪሳዊያንም እዚያ መቃብሩ ጋ ካዩን ጉዳት ያደርሱብናል በማለት አልፈሩም፣ ድካማቸውና የሽቶውን ወጪ ከምንም አልቆጠሩም፡፡ ይህ ሁሉ መሰናክል ሊሆን የሚችል ነገር እያለ ወደ ፊት ሲጓዙ በመጨረሻ ድንጋዩም ተንከባሎ አገኙት፡፡ መግደላዊት ማርያም ከእርሷ ጋር የነበሩት ሴቶች መቃብሩ ባዶ እንደሆነ አይተው መላእከቱ ያሏቸውን ሰምተው ሲመለሱ እርሷ ግን ጌታ ኢየሱስን ከመውደዱ የተነሳ እዚያው ቆይታ እያለቀሰች የኢየሱስን አስከሬን ስታፈላልግ በመቆየቷ ሕያው ሆኖ ተግልጦላት እዚያው ቦታ ላይ አየችው፡፡ አብረዋት ከነበሩት ቅዱሳን ጨመር አድርጋ የሰራችው ስራ ልዩነት አመጣላት፡፡ ማቴ 28፡1-10፣

3. ተከታታይነት ያለው/ጥብቅ (መልስ እስከሚመጣ የሚቀጥል) ጸሎት፡-
*መኃ መኃ 4፡6፣ ነህ ከመቅደዱ በፊት ጥላውም ሳይሸሽ፣ ወደ ከርቤው ተራራ ወደ ዕጣኑም ኮረብታ እወጣለሁ።*

*ያዕ 5፡17-18፤ ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።*

*ጸሎቱ በልብ መክበድ/መጫጫን/ሀዘን፣ ማጉረምረም፣ ሙግት፣ ወቀሳ ያልተቀላቀለበት ሊሆን ይገባል- ምክንያቱም ምንም አይነት ከባድ ችግር ውስጥ ብንሆን የችግሩ መንስኤ እግዚአብሔር አይደለምና፡፡*
*መዝ 95፡1፣ 66፡1፣ 98፡4፣8፣ ኢሳ 61፡3)፣ በእምነት ጽናት፣ በትህትናና አክብሮት፣ ደስታ በተሞላ በምስጋና፣ ሳያቋርጡ መልስ እስከሚገኝ እግዚአብሔርን የምትማጸኑ ሰዎች ትኖራላችሁ፡፡* ያልጀመርንም ሆነ ጀምረን የተዘናጋን አጠናክረን እንጀምር፡፡ ግዚአብሔርም መልካም አምላክ ከጠበቅነው በላይ የሆነ ታምራዊ ኃይሉና በጎነቱን ያሳየናል፡፡ ጊዜያዊ ችግሮቻችን ሳንዋጋቸው ቀርተን ቋሚ ሆነው ከኛ ጋር እየጨመሩ በመሄድ ከሚኖሩ ከፍታ ላይ በመውጣት ብንዋጋቸው ይሻላል፡፡

የውሃ እንፋሎት ከምድር እየተነሳ ሰማይ ላይ በደመናነት ቀስ በቀስ እየተከማቸ መልሶ ዝናብ ሆኖ እንደሚወርድ እንዲሁ ተከታታይነት ያለው ጸሎታችሁ በጊዜው መልስ ይዞ ይመጣል፡፡ የጌታን ክብር ማየት ያስችላል፡፡ ጸሎት በስጋ ኃይል ብቻ ከሆነ ታላቅ ሸክም ይሆናል፡፡ ስለዚህ የመንፈስ ቅዱስ እርዳታ መጠየቅ ተገቢ ነው፡ ፡
ያዕ 4፡6፣ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል ለትሁታን ግን ጸጋን ይሰጣል፡፡ እግዚአብሔር መልካም ነገር የሚያደርግልን እርሱ የኛ አገልጋይ ሊሆን ስለተገባን ወይም የኛ ዕዳ ስላለበት ሳይሆን ከራሱ መልካምነት የተነሳ ጸጋውን ሊያበዛልን ወዶ

መሆኑን በመረዳት የጸሎታችን መልስ ካልፈጠነ አምካችን በራሱ ጊዜ የለመንነውን እንደሚሚጠን መጠበቅ አለብን፡፡

4. እምነትና ምስክርነት፣ ሮሜ10፡6-10፣ እኛ አምላካችንን ለማየት ወደ ሰማይ መውጣት- የማይቻለን ነገር፣ ባህር ማዶ መሻገርም (ኢየሩሳሌም መሄድ የሚቻል በሆንም ቀላል አይደለም) አልተጠየቅንም፡፡ ተጽፎ የተቀመጠልንን ወንጌል በልባችን አምነን በአፋችን መመስከር ነው፡፡
   ምስክርነት (testimony, witnessing) ሐሥ 1፡8 ምስክርነት ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ ለብሶ በምድር በተመላለሰበት ጊዜ አብረውት የነበሩ ደቀመዛሙርት እሰከ ሞትና ትንሳኤው ድረስ ሲያደርግ፣ ሲናገርና ሲሰራ ያዩትን የአይን ምስክርነት፤ በመጽሐፍ ቅዱስ አስፍረው ያቆዩልንን አምነን፣ እንዲሁም እኛ በአሁኑ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች ጌታን ከተቀበልን በኋላ በግል ሕይወታችን ጌታ ያደረገው ነገር መመስከር እንዲሁም በ3ኛነት በመጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለኛ አደረገ የሚለውን አምነን ተቀብለን ያንኑ መልሰን በአፋችን መናገርን/መመስከርን ያመለክታል፡፡ 1ሳሙ 17፡37፣ ራዕ 12፡11?
   አንዴ ከጠላት ጋር ውጊያ ከጀመሩ በጭራሽ ጀርባን ለጠላት መስጠት/መጠራጠር/ተስፋ መቁረጥ ወደኋላ ማፈግፈግ አይገባም፤ ይሄ በመከላከያ የልተሸፈነውን ሰውነታችን እንዲያጠቃ በር በመክፈት ለጠላት አጅ እንደመስጠት ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት መንፈሳዊ ከፍታዎች ላይ በመውጣት ጌታ ኢየሱስን ሊያዩት ለሚጠባበቁት ሁሉ ዘኬዎስ ቤት እንደሆነው ሁሉ የእግዚአብሔር ልዩ ጉብኝትና ባርኮት፣ ፈውስና ከጠላት ክፉ ተጽዕኖ ሁሉ መዳን ይሆንላቸዋል። አሜን!!!